## <u>ብርቱካን ፡ ሆንሽ ፡ ሬት ፤</u>

የአገራችን ፡ አየር ፡ ለኑሮ ፡ ተስማሚ ፣
ምግብ ፡ ቢያጥረን ፡ እንኳ ፡ እንመጣለን ፡ ሎሚ ።
የርሃብ ፡ ማስታገሻ ፡ አናጣም ፡ ትርንጐን ፣
ገና ፡ ከመግባቷ ፡ ስናያት ፡ ብርቱካን ፣
ከከጀላትማ ፡ ጠውልጋ ፡ ልትመክን ።
በደንብ ፡ ሳያጤኑ ፡ ውሃ ፡ ቢያጠጧት ፣
ልድረቅ ፡ ልድረቅ ፡ አለች ፡ ነፋሱ ፡ አዋክቧት ።
ተጠራጥረን ፡ ነበር ፡ ገና ፡ በለጋዋ ፣
ከአገሯ ፡ ሳትወጣ ፡ በዝቶ ፡ ስጦታዋ ፤
ዐወቅሽ ፡ ዐወቅሽ ፡ ቢሏት ፡ መጽሐፍ ፡ ልጠብ ፡ አለች ፣
ብርቱካን ፡ ጭማቂ ፡ እያንጠበጠበች ።
ቅንጅት ፡ ፍቅር ፡ ነው ፡ ስትይ ፡ ቆይተሽ ፣
ምን ፡ አስነኩሽና ፡ ቃልሽን ፡ አጠፍሽ ።
ኃይሉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነው ፡ ሴት ፡ ሆንሽና ፡ ከዳሽ ፣
ለአገር ፡ ቤት ፡ ወገንሽ ፡ ምንድን ፡ ይሆን ፡ መልስሽ ፣
አመሪካ ፡ ገብተሽ ፡ ሙጥኝ ፡ ለማለትሽ ፣
ለኒያ ፡ ነብስ ፡ ገዳዮች ፡ ወያኔ ፡ አጋሮችሽ ፣
ብርሃኑ ፡ ነጋ ፡ ብሩክ ፡ ሲባልልሽ ፣
ትንሹ ፡ ኃሉና ፡ ግዛቸው ፡ ከበወሽ ፣
ድንገት ፡ ሳታስቢው ፡ ቀኑ ፡ ጨለመብሽ ።
ሆያ ፡ ሆየ ፡ እያሉ ፡ ሲያጨበጭቡልሽ ፣
ወይ ፡ አለማወቅሽ ፡ ለወደፊት ፡ ዕጣሽ ፣
ወጣት ፡ ወጣት ፡ እያልሽ ፡ እያሳሳቱሽ ፣
ለመሪዋ ፡ ኢትዮጵያ  ፡ ማሰብ ፡ ከተሳነሽ ፣
በይ ፡ እርምሽን ፡ አውጭ ፡ ግዜው ፡ ሳይመሽብሽ ።
ብርቱካንነትሽ ፡ መዓዛቅው ፡ ከቀየረ ፣
ሆድ ፡ ብሶን ፡ መሮናል ፡ ሳናይሽ ፡ በቀረ ፤
ለክፉ ፡ ቀን ፡ ግዜ ፡ ካልሆንሽ ፡ ለሕዝባችን ፣
ለነፃነት ፡ ካልቆምሽ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ አገራችን ፣
ድምፅ ፡ በማለስለስ ፡ ቀርቅረሽ ፡ አንገትሽን ፣
ለመኖር ፡ ከሆነ ፡ ጥገት ፡ አርገሽ ፡ እኛን ፣
ሥራሽን ፡ ፈልጊ ፡ ጥፊ ፡ ከፊታችን ።
የአመሪካ ፡ መሬት ፡ ስላለው ፡ አባዜ ፣
ዘወር ፡ በይ ፡ አንይሽ ፡ አታብኸር ፡ ኑዛዜ ፣
ብርቱካን ፡ ሆንሽ ፡ ሬት ፡ ገጥሞናል ፡ ትካዜ ።

***መሪያችን ፡ ኃይሉ ፡ ነው ። ከቅንጅት ፡ ጋር ፡ ወደፊት! ኢትዮጵያና ፡ ቅንጅት ፡ ያሸንፋሉ!!!!!!!!!! ። ወደፊት!.....ወድፊት!!.....አሁንም ፡ ወደፊት!!!.............***

*መስከረም ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ፳፻ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ።*